ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
FORUM FOR SOCIAL STUDIES (FSS)

# እ.ኤ.አ. 2019 ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

## ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

## FORUM FOR SOCIAL STUDIES (FSS)

# እ.ኤ.አ. 2019 ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት

ነሐሴ 8 ቀን 2012 ዓ.ም (14 July 2020)

## ማውጫ


**መግቢያ** ............ 4

**1. የዓመቱ ድርጅታዊ ክንዋኔዎች** ............ 5

1.1 ሃያ አንደኛው ጠቅላላ ጉባዔ -መጋቢት 21 ቀን 2011 (30 March 2019) ............ 5
1.2 አምስተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እና ውጤቶቹ - መስከረም 10 ቀን 2012 (21 September 2019) 6
1.3 የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎች እና ውጤቶቻቸው ............ 7

**2. የድርጅቱ ሥርዓታዊ ሁኔታ እና ሕጋዊ ዕውቅና** ............ 9

**3. የሠራተኛ አስተዳደር ጉዳይ** ............ 9

**4. የድርጅቱ ሕንፃ ግንባታ ሂደት** ............ 10

**5. የተጠናቀቁ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች** ............ 10

5.1 የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች ............ 11

**6. ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በጋራ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች** ............ 12

6.1 ሴቶችን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያብቃትን ለማዳበር የሚረዳ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት (Evidence-based capacity development project for women Socio-economic Empowerment) ............ 12
6.2 የአየር ንብረት ለውጥና የሰዎች እንቅስቃሴ (Governing Climate Mobility -GCM) ............ 13

**7. የህዝባዊ ውይይት መድረክ መርሃ-ግብር** ............ 13

7.1 ዲሞክራሲያዊ ጉዞ ለውጦች፡- በዋና ዋና አገራዊ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለውጦች ላይ የሚደረግ የሕዝባዊ ውይይት መድረክ (Clarifying the Uncharted Routes of Ethiopia's Transition towards Democracy: ...) ............ 14
7.2 መሬት፤ የመሬት አጠቃቀም እና የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ፡- ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ (Land, Land Utilization and Food Security in Ethopia: A Public Dialogue Forum Series) ከታህሳስ 16 – መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም (26th December 2019 — 2nd April 2020) ............ 15

**8. የሚዲያ ሥርጭት እና የኮምዩኒኬሽን መርሃ-ግብር** ............ 15

8.1 የኤፍ.ኤስ.ኤስ የጥናት/ምርምር እና የውይይት መድረክ ውጤቶች የሚዲያ ሥርጭት ፕሮጀክት (Dissemination of FSS Research and Dialogue Outputs through the Media) ............ 16
8.2 ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች፥ እንድምታዎቻቸው እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ … (Clarifying the Uncharted Routes of Ethiopia's Transition towards Democracy:…) በተሰኘው ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ፕሮጀክት አካል በመሆን በተካሄዱት የውይይት መድረኮች ላይ የተመሰረቱ የሬዲዮ ፕሮግራሞች ለሕዝብ ተደራሽ ሆነዋል። ............ 16
8.3 የዋይድ ሕዝባዊ ግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሚዲያ ሥርጭት ፕሮጀክት (WIDE Awareness and Media Dissemination Project) በኤፍ.ኤስ.ኤስ እና በ"Ethiopia-WIDE: Well-Being Ill-Being Dynamics in Ethiopia በተሰኘ አጋር የጥናት ማዕከል በመተባበር የተካሄደ ሲሆን፤ የጥናት ማዕከሉ በተለያዩ የልማትና ልማት-ነክ ጉዳዮች ከ20 ዓመት በላይ በወሰደ ግዜ ያካሄዳቸው ጥናት ዉጤቶች ቀጥለው በተዘረዘሩት የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ለሕዝብ ተደራሽ ሆነዋል። ............ 16
8.4 ከ CAFOD, SCIAF, Trocaire (CST) ጋር በመተባበር በሚተገበረው በሴቶች ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብቃትን ለማዳበር የሚረዳ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ (Evidence-based Capacity Development Project for Women Socio-economic Empowerment) ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ፤ ............ 17

9. **የሕትመትና የኦድዮ-ቪድዮ ሥራዎች** ....... 17

9.1 መጻሕፍትና ሞኖግራፎች ....... 17
9.2 የፖሊሲ ፍሬ ኃሳብ ሕትመት (Policy Briefs) ....... 17
9.3 ብሮሹር እና ኦዲዩ-ቪዲዮ ....... 18
9.4 የአፍሪካ መፅሐፍት ግምገማ (African Review of Books-ARB) ....... 18

10. **የቤተ-መፅሀፍት እና የዲጂታል ኮሚኒኬሽን አገልግሎት** ....... 18

11. **የውጭ ትብብር እና ተሳትፎ** ....... 19

12. **ጥንካሬ፣ ያጋጠሙ መልካም አጋጣሚዎች እና ተግዳሮት** ....... 20

## መግቢያ

ይኽ የኤፍ.ኤስ.ኤስ. ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት የሚሸፍነው ጊዜ እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 2019 መጀመሪያ እስከ ዲሴምበር 2019 መጨረሻ ያለውን ሙሉ እንድ ዓመት ነው። በመደበኛው አሠራር ሪፖርቱ፤ በማኔጅመንቱ ተረቆ እና በሥራ አመራር ቦርዱ ታይቶ ለድርጅቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በመቅረብ መፅደቅ ያለበት የካላንደር ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወራት ውስጥ ነበር። ሆኖም፤ በሁለት ምክንያቶች የተነሳ በዚህ ዓመት የጊዜ ሠሌዳ ማክበርና መደበኛውን የአፀዳደቅ ሥርዓት መከተል አልተቻለም። የጊዜ ሠሌዳውን መጠበቅ ያልተቻለበት ምክንያት በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከቀድሞው GAAP ሂሳብ አያያዝ ዘመናዊና ጠቃሚ ወደ ሆነው IPSAS የተደረገው ውስብስብ ሽግግር የጠየቀው ረዥም ጊዜ ሲሆን፤ መደበኛውን የአፀዳደቅ ሥርዓት መከተል ያልተቻለው ደግሞ የኮሮና ወረርሽኝን ለመግታት ጠቅላላ ጉባዔን የመሰለ ከሠላሳ ሰዎች በላይ የሚያገናኝ ስብሰባ እግድ ያለበት በመሆኑ ነው። የማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች የፈጠሩትን አስገዳጅ ሁኔታ ተረድቶ ይሁንታውን በመለገሡ፤ ይኽ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በሥራ አመራር ቦርዱ 71ኛ ስብሰባ በነሐሴ 8 ቀን 2012 (እ.ኤ.አ ኦገስት 14 ቀን 2020) ፀድቆ የድርጅቱ ሕጋዊ ሠነድ ሆኗል።

## 1. የዓመቱ ድርጅታዊ ክንዋኔዎች

በኤፍ.ኤስ.ኤስ መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ እንደሰፈረው፤ መደበኛ አባላቱ በእኩልነት የሚሳተፉበት የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የበላይ ወሳኝ አካሉ እንደመሆኑ እና ጠቅላላ ጉባዔ ባልተሰበሰበት ወቅት ደግሞ በሱ የተመረጡ ዓባላትን የሚያቅፈውና ለሱ ተጠሪ የሆነው የሥራ አመራር ቦርዱ ቀጣይ ወሳኝ አካሉ እንደመሆኑ፤ የኤፍ.ኤስ.ኤስን ዋነኛ ዓመታዊ ድርጅታዊ ለመዳሰስ በዓመቱ ውስጥ ከተካሄዱት መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች እንዲሁም ከሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባዎች ሂደቶችና ውሳኔዎች መጀመርን ግድ ይላል።

### 1.1 ሃያ አንደኛው ጠቅላላ ጉባዔ -መጋቢት 21 ቀን 2011 (30 March 2019)

ኤፍ.ኤስ.ኤስ ሃያ አንደኛ ጠቅላላ ጉባዔውን መጋቢት 21 ቀን 2011 አካሄደ። በዚህ ጉባኤ የኤፍ.ኤስ.ኤስ የሥራ አመራር ቦርድ ሊቀ-መንበር የሆኑት ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት፣ የጠቅላላ ጉበኤ ሰብሳቢ ዶ/ር ወሰኑ ይማም እና ፀሐፊው አቶ አሳብነህ ሞላ ለሥራ ከከተማው ውጭ በመሆናቸው በምክንያት መገኘት እንዳልቻሉ ካሳወቁ በኃላ ጉባኤው ጊዜያዊ ሰብሳቢና እና ፀሐፊ እንዲመርጥ ኃሳብ አቅርበው ከጉባኤው ተሳታፊዎች ፐ/ር ሽፈራው በቀለ በጊዜያዊ ሰብሳቢነት እና ወ/ት ዓለምገና ገብረዮሐንስ ደግሞ በጊዜያዊ ፀሐፊነት በሙሉ ድምፅ ከተመረጡ በኃላ፤ የእለቱ ጊዜያዊ ሰብሳቢ ፐ/ር ሽፈራው ምልዐተ ጉባኤ መሟላቱን በማረጋገጥ እና በሥራ አስፈፃሚው ቦርድ ተረቅቆ የቀረበው የዕለቱ አጀንዳ በማፀደቀ፤ ሰብሰባው እንዲጀመር አደረጉ። በመቀጠልም፤ በዕለቱ ጊዜያዊ ሰብሳቢ መሪነት እና በጊዜያዊ ፀሐፊነት ስብሰባው ቀጥሎ የሚከተሉትን ተግባራት አከናወነ።

1. የ20ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ ጉባዔ በንባብ ተሰምቶ ፀደቀ፤
2. ከቃለ ጉባዔው በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ወይይት ተካሄደ፤
3. እ.ኤ.አ የ2018 ዓመት የሥራ ሪፖርት በሥራ አስፈፃሚው ቦርድ ሊቀመንበር ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት በንባብ ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበት ፀደቀ፤
4. እ.ኤ.አ የ2018 የበጀት ዓመት የሒሳብ ሪፖርት በሰለሞን እሸቴና ጉዋደቹ የተመሰክረላቸው ሂሳብ አዋቂዎች በተሰኘው ሂሳብ መርማሪ ድርጅት ቀርቦና ውይይት ተካሂዶበት ፀደቀ፤
5. እ.ኤ.አ የ2019 የበጀት ዓመት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ረቂቅ በሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ በዶ/ር የራስወርቅ አድማሴ ቀርበውና ውይይት ተካሂዶባቸው ፀደቁ፤
6. የማኅበሩ ደንብ የሚፈቅደውን የአገልግሎት ዘመን በማገባደዳቸው እና በመኖሪያ ቦታ ዝውውር የተነሳ መተካት ያለባቸውን የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን የሚተኩ ዶ/ር አሰፋ በቀለ፣ ዶ/ር አበጀ ብርሃኑ፣ ወ/ሮ ትዕግሥት ተፈራ እና ዶ/ር እሸቱ በቀለ በድምፅ ብልጫ ተመረጡ፤
7. የአባልነት ጥያቄያቸው መሟላቱ በሥራ አመራር ቦርዱ ተጣርቶ የቀረበውን የዶ/ር አስናቀ ከፈለ እና የዶ/ር አበበ አሰፋ አባልነት አፀደቀ።

## 1.2 አምስተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እና ውጤቶቹ - መስከረም 10 ቀን 2012 (21 September 2019)

ኤፍ.ኤስ.ኤስ በሀያ ዓመት ዕድሜው አራት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎችን ጠርቷል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች በሰኔ 24 ቀን 1998፣ መስከረም 30 ቀን 2001 እና በሚያዝያ 1 ቀን 2003 የተጠሩ ሲሆኑ፣ አራተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እየተባባሰ በመጣው የድርጅቱ የፋይናንስ አቅም ላይ ለመነጋገር የተጠራ እና በጥቅምት 10 ቀን 2011 ተካሂዶ የነበረው ነው፡፡ ይህ ጉባዔ የተወያየባቸው ሁኔታዎችና የደረሰባቸው ውሳኔዎች ብዙም ሳይቆይ አዲስ በወጣውና በእጅጉ በተሻሻለው የሲቪል ማኅበራት አዋጅ ፈፅመው በመታለፋቸው የተነሳ በዚህ የሪፖርት ዓመት ማለትም በመስከረም 10 ቀን 2012 (21 September 2019) የአምስተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔን መጠራት አስፈለገ፡፡

አምስተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በማኅብሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ፣ ዶ/ር ወሰኑ ይማም እና የዕለቱ ጊዜያዊ ፀሐፊ እንዲሆኑ በተመረጡት በዶ/ር አበበ አሰፋ አማካይነት ሁለት የስብሰባውን ዋና ጉዳዮች፤ ማለትም የማኅበሩን የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ መርምሮ ማፅደቅን እና የሥራ አመራር ቦርዱን በምርጫ ማሟላትን ተግባራት አከናውኗል፡፡

### *1.2.1 የማኅበሩን የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ መርምሮ ማጽደቅ*

ለውይይት የቀረበው የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ ማኔጅመንቱ በመጋቢት 3 ቀን 2011 ዓ.ም. የወጣው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር1113/2011 (Proclamation No. 1113/2019) በሚደነግገውና ከኤጀንሲው በተላለፈለት የምዝገባ መመሪያ መሠረት በጥንቃቄ ያዘጋጀውን አንደኛ ረቂቅ የመተዳደሪያ ደንብ ለአባላቱ በመላክ እንዲተቹበት በማረድጉ እና በመቀጠልም አባላት በሰጧቸው ግብአቶች የበለፀገ ሁለተኛ ረቂቅ ተዘጋጅቶ እና በሥራ አመራር ቦርዱ አጸድቆ ከዚህ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ጋር በእንደገና ለአባላት የተላከ በመሆኑ፤ በዚህ አሳታፊ በሆነ ሂደት አማካይነት የስብሰባው ተሳታፊዎች በቂ ዝግጅት አድርገው የመጡ በመሆኑ ፍሬያማ የማሻሻያ ውይይት ተካሂዶ ለማኅበሩ የወደፊት እድገት መሠረት የሚሆን መተዳደሪያ ደንብ ለማፅደቅ ተችሏል፡፡

እያንዳንዱ ረቂቅ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፆች ተራ በተራ እየቀረቡ አስተያየት እየተሰጠባቸው ውይይት እየተካሄደባቸው እና በሙሉ ስምምነት እየተሻሻሉ ተቀባይነታቸው አንድ ባንድ ተረጋገጠ፡፡ ማሻሻያዎቹም በሙሉ በእለቱ የጉባዔው ፀሐፊ እየተመዘገቡ ተስተካክለው የመጨረሻ ውጤት የሆነውም መተዳደሪያ ደንብ ለስብሰባው ቀርቦ በሙሉ ድምፅ በመጽደቁ የጉባኤው ሰብሳቢና የእለቱ የጉባዔው ፀሐፊ የፈረሙባቸው እና የማኅበሩ ማሕተም የተደረገባቸው ሦስት ቅጅዎቹ፤ በእለቱ የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የተገኙት አባላት ከፈረሙበት የተሳታፊዎች ሰንጠረዥ ጋር ተያይዞ የድርጅቱ ዋና ሰነድ በመሆን እንዲመዘገብ በሙሉ ድምፅ ተወሰነ፡፡

### *1.2.2 የሥራ አመራር ቦርዱን በምርጫ ማሟላት*

ከላይ የተመለከተውና በአዲስ የጸደቀው የመተዳደሪያ ደንብ የማኀበሩ ሥራ አመራር ቦርድ ሰባት አባላት ይኖሩት ዘንድ ስለሚደነግግና ከዚህ በፊት ተመርጠው በማገልገል ላይ ያሉት ሰዎች ስድስት ብቻ ስለሆኑ አንድ ተጨማሪ የሥራ አመራር ቦርድ አባል መምረጥ በማስፈለጉ በሰብሳቢው ተወስቶ መተዳደሪያ ደንቡ በሚያዘው የምርጫ ሥርዓት መሰረት ወ/ት አለምገና ገብረዮሃንስ ለሚቀጥሉት ሦስት አመታት በሥራ አመራር ቦርዱ እንድታገለግል በሙሉ ድምፅ ተመረጠች።

## 1.3 የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎች እና ውጤቶቻቸው

በሪፖርት ዓመቱ የኤፍ.ኤስ.ኤስ ሥራ አመራር ቦርድ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በሚያዘው መሠረት አራት መደበኛ ስብሰባዎችን ማድረግ ሲጠበቅበት ሳለ፤ ሦስት ስብሰባዎችን ብቻ አካሂዷል። ይኸም የሆነባቸው ምክንያቶች፤ ማኔጅመንቱ ቅድሚያ ይሰጣቸው ዘንድ አስገዳጅ የሆኑት የድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ አርቅቆ ተጨማሪ የሆነውን አምስተኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት እና በዚህ ጉባዔ የፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብ ለኤጀንሲው አስገብቶ ማፀደቅና የምዝገባ ምስክር ወረቀት የማግኘቱ ሥራዎች አንቀው ስለያዙት ነው።

የዓመቱ የመጀመሪያው ስብሰባ የሆነው 68ኛው መደበኛ **የሥራ አመራር ቦርድ** ስብሰባ በመጋቢት 19 ቀን 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በማርች 28 ቀን 2019)፣ ሁለተኛ የሆነው 69ኛው ስብሰባ በጳጉሜ 1 ቀን 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በሰብቴምበር 6 ቀን 2019)፣ ሦስተኛው ደግሞ በታህሣሥ 6 ቀን 2012 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በዲሴምበር 16 ቀን 2019) ተካሂደዋል።

ከሃያ አንደኛው ጠቅላላ ጉባዔ ቀደም ብሎ በመጋቢት 19 ቀን 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ. በማርች 28 ቀን 2019) የተካሄደው **68ኛው መደበኛ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ** በዋነኛነት ያተኮረው ለጠቅላላ ጉባዔው የሚቀርቡትን ሀ/ የጉባዔውን ረቂቅ አጀንዳ ለ/ የማኀበሩን መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ ሐ/ እ.ኤ.አ የ2018 የበጀት ዓመት የሥራ ሪፖርትን ረቂቅ መ/ እ.ኤ.አ የ2019 የበጀት ዓመት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀትን ረቂቅ ሠ/ የእጩ አባላትን ዝርዝር አጣርቶ በመወሰን ላይ ነበር።

ይኸው 68ኛው መደበኛ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ ከላይ ከተጠቀሱት ክንዋኔዎቹ በተጨማሪ በሁለት ሠራተኞቹን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጥቷል። የመጀመሪያው ውሳኔ፥ የድርጅቱ ተቀጣሪ የምርምር ሠራተኞቹ ወደ ድርጅቱ በሚያመጧቸው የምርምር ፕሮጀክቶች ውስጥ ለቦርዱ አመልክተውና ይሁንታውን አግኝተው በትርፍ ጊዜያቸው በመሳተፍ ተጨማሪ ክፍያ የሚያገኙበትን መንገድ የሚከፍት አግባብ መፍቀድን የሚመለከት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የድርጅቱ ሴት ሠራተኞች የወሊድ ዕረፍት ከሦስት ወደ አራት ወራት መራዘምን የተመለከተ ነው። (ዝርዝሩ በድርጅቱ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ቃለ-ጉባዔ ቁጥር 68 ውስጥ ተመልክቷል)

**በሪፖርት ዓመቱ ሁለተኛ የሆነው 69ኛው የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ** በጳጉሜ 1 ቀን 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በሰብቴምበር 6 ቀን 2019) ተገናኝቶ፤ በዋነኛነት ከላይ የአምስተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በተዘገበበት ቁጥር 1.2 ተራ ቁጥር 1 ስር ሂደቱ በዝርዝር የተወሳውን የድርጅቱን አዲስ ረቂቅ የመተዳደሪያ ደንብ ለመጨረሻ ጊዜ አፅድቆ ለማጎበሩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ እንዲፀድቅ፤ ለዚህም ሲባል አምስተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ለመስከረም 10 ቀን 2012 (21 September 2019) እንዲጠራ ወሰነ።

ይኸው በሪፖርት ዓመቱ ሁለተኛ የሆነው 69ኛው ሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ በተጨማሪ ሀ/ በድርጅቱ የገንዘብ እጥረት የተነሳ ለረዥም ጊዜ ምላሽ ሳያገኝ ቆይቶ የነበረውን የሠራተኞች ወርሃዊ ደሞዝ የማሻሻል ጉዳይ በተመለከተ፤ የድርጅቱ የገቢ ፍሰት በተጨባጭ መሻሻልን ተከትሎ ከሁለት እስከ አራት ዓመታት ምንም ማሻሻያ ላላገኙት የምርምርና የአስተዳደር ሠራተኞች በአማካይ የሃያ በመቶ (20%) ጭማሪ፤ በየዓመቱ ጭማሪ ሲደረግላቸው ለቆዩት ድጋፍ-ሰጭ ሠራተኞች ደግሞ የአስር በመቶ (10%) ጭማሪ እንዲደረግላቸው ወስኗል። ለ/ የሦስት እጩ አባላትንም ማመልከቻ መርምሮ በማፅደቅ ጉዳዩ በመደበኛ እንጅ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ የማይታይ አይነት እንደመሆኑ ፎርማል ውሳኔው 22ኛውን ጠቅላላ ጉባዔ መጠበቅ እንደሚኖርበት አስምሮበታል። (ዝርዝሩ በድርጅቱ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ቃለ-ጉባዔ ቁጥር 69 ውስጥ ተመልክቷል)

**በሪፖርት ዓመቱ ሦስተኛ የሆነው 70ኛው የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ** ደግሞ በታህሣሥ 6 ቀን 2012 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በዲሴምበር 16 ቀን 2019) ተካሂዷል። ሀ/ በ69ኛው ሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ ላይ ማኔጅመንቱ አዘጋጅቶ አቅርቦ ሳለ በፅሞና ለማየት ሲል በይደር አቆይቶት የነበረውን ረቂቅ የድርጅቱን የግዥና የንብረት አስተዳደር ማኑዋል (Procurement and Property Management Manual) ስብሰባው መርምሮ ሲያፀድቅ፤ ከዚህ በተጨማሪም ለአስር ዓመታት ያህል ሳይሻሻል በመቆየቱ የተነሳ ለሥራ ማነቆ እየሆነ የመጣውን የድርጅቱን የባለሙያዎች ክፍያና የውሎ አበል መጠን ሰንጠረዦች በማሻሻል በማኔጅመንቱ ተሰርቶ የቀረቡለትን ረቂቅ ሰንጠረዦች መርምሮ ከቀኑ ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውሉ ወስኗል።

ይኸው 70ኛው የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፤ ጊዜው በፈጠረው ፈጣን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የተነሳ፤ ከሕትመት መረጃ ዝውውርና አጠቃቀም ይልቅ የኤሌክትሮኒኩ ዘርፍ እያየለ በመምጣቱ፤ የድርጅቱ መፃህፍት ቤት ተጠቃሚዎች ቁጥር እያሽቆለቆለ የሚሰጠውም አገልግሎት እየደበዘዘ እንዲሄድ በማድረጉ "የኤፍ.ኤስ.ኤስ. መፃህፍት ቤት ኃላፊን" የሥራ መደብ (position of FSS Librarian) ወደ የኤፍ.ኤስ.ኤስ መፃህፍት ቤት እና የዲጅታል ግንኙነት ኃላፊ የሥራ መደብ (position of FSS Librarian and Digital Communication Officer) እንዲቀየርና ከስያሜ ለውጡ ተያያዥ የሆነውን በማኔጅመንት ኮሚቴው የተዘጋጀ የሥራ ዝርዝር ጭምር አፅድቋል። (ዝርዝሩ በድርጅቱ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ቃለ-ጉባዔ ቁጥር 70 ውስጥ ተመልክቷል)

## 2. የድርጅቱ ሥርዓታዊ ሁኔታ እና ሕጋዊ ዕውቅና

ኤፍ.ኤስ.ኤስ. ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ባሳለፋቸው ሃያ አንድ ዓመታት ውስጥ ተለዋዋጭ ዓለም አቀፋዊ እና ሃገራዊ ሁኔታዎች በጠየቁና በፈቀዱ ዋነኛ ከሆነው የመተዳደሪያ ደንቡ ጀምሮ የተለያዩ ዝርዝር የአሠራርና የአስተዳደር ደንቦችንና ሕግጋትን እንዲሁም የረዥምና የአጭር ጊዜ የዕቅድ ሠነዶችን እያዘጋጀ ድርጅታዊ ሥርዓቱን ሲገነባ ቆይቷል፡፡ በዚህ ረገድ፤ የሪፖርት ዓመቱ፤ ድርጅታችን ከፍተኛ ስኬት ያስመዘገበበት ወቅት ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ሃያ አንደኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ አምስተኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እናም የሥራ አመራር ቦርዱ ባካሄዳቸው ስብሰባዎች አማካይነት፤ የቆመላቸውን ዓላማዎች ይበልጥ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚረዱ ማሻሻያዎችና ተጨማሪዎች በማካተት መተዳደሪያ ደንቡን ከመሠረቱ ሲያሻሽል አዲስ የግዥና የንብረት አስተዳደር ማኑዋል እና የተሻሻለ የባለሙያዎች የክፍያና የውሎ ዓበል ገበታ አውጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡

ኤፍ.ኤስ.ኤስ. በሪፖርት ዓመቱ ካስመዘገባቸው ዋነኛ ስኬቶች መካከል የድርጅቱን ሂሳብ አያያዝ የማዘመን ሥራው ይገኛል፡፡ መንግሥት በሰጠው መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሂሳብ አያያዝ ከነባሩ የGAAP ስልት ወደ IPSAS በማሸጋገር የሪፖርት ዓመቱ የሂሳብ ምርመራና የሂሳብ ሪፖርት በIPSAS ስልት እንዲከናወን ከፍተኛ ርብርቦሽ ተካሂዶ ተሳክቷል፡፡ ይኸም IPSAS-መር ሪፖርት ከዚህ የሥራ ክንዋኔ ሪፖርት ጋር የቀረበ ነው፡፡

በመጨረሻ፤ የሪፖርት ዓመቱ የኤፍ.ኤስ.ኤስ ስኬቶች ቁንጮ ሆኖ ሊወሰድ የሚገባው ድርጅቱን በሰፊው ሊያሠራና ሊያራምድ የሚችል የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንቡ በጥቅምት 4 ቀን 2012 (እ.ኤ.አ ኦክቶበር 15, 2019) በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ፀድቆ በዚሁ ቀን ሕጋዊነቱን የሚያረጋግጠውን የምዝገባ ምስክር ወረቀት መረከቡ ነው፡፡

## 3. የሠራተኛ አስተዳደር ጉዳይ

ከሪፖርቱ ዓመቱ አስቀድሞ በነበሩት ዓመታት እየቀነሰ የመጣው የፕሮፌሽናል ሠራተኞች ብዛት ችግር ተባብሶ ነበር፡፡ የሥርዓተ-ፆታና ልማት ስፔሽያሊስት ሆና በቅንነት ስታገለግል የቆየችው ባለሙያ የአራት ወራት የወሊድ ዕረፍት ጊዜዋን ጨርሳ ወደ ሥራ ገበታዋ ትመለሳለች ተብሎ ስትጠበቅ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከድርጅቱ ጋር የምትገናኝባቸውን መስመሮች በመዝጋት ለወራት ጠፍታ በዚያው በመቅረቷ፤ ማኔጅመንቱ በከፍተኛ ችግር ወራት ካስቆጠረ በሁዋላ በነሐሴ 2019 በአዲስ ተቀጣሪ ባለሙያ የሥራ ቦታውን ለመሸፈን በቅቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፤ በድርጅቱ ውስጥ ለስምንት ዓመታት በሶሲዮ-ኤኮኖሚክ ሲኒዮር ተመራማሪነት እና በምርምር ሕትመትና አስተዳደር ሥራዎች ሁለ-ገብ ድጋፍ-ሰጭ በመሆን ያልተቆጠበ አገልግሎታቸውን ሲያበረክቱ የቆዩት ዶ/ር ዘሪሁን መሀመድ በሚቀጥለው የሪፖርት ዓመት (እ.ኤ.አ 2020) መባቻ ላይ ከድርጅቱ የሚሰናበቱ መሆናቸውን በማሳወቅ ማኔጅመንቱ ይህንን ተገንዝቦና ጊዜ ወስዶ እሳቸውን የመተካት እንቅስቃሴ እንዲያደርግ አሳስበዋል፡፡ ማኔጅቱም ይኸንኑ ለሥራ አመራር ቦርዱ በማስታወቅ ብቁ ባለሙያ የማፈላለጉን

እንቅስቃሴ የጀመረ ቢሆንም በዓመቱ መዝጊያ ላይ በተከሰተው የኮሮና-19 ወረርሺኝ ሳቢያ ሂደቱ ተደናቅፎ ይገኛል።

የሠራተኞቹን ሁኔታ በተመለከተ ኤፍ.ኤስ.ኤስ በሪፖርቱ ዓመት ደሞዝን በማሻሻል በጎ እርምጃ ለመውሰድ ችሏል። በጳጉሜ 1 ቀን 2011 (እ.ኤ.አ ሰብቴምበር 6 ቀን 2019) የተሰበሰበው 69ኛው ሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ በድርጅቱ የገንዘብ እጥረት የተነሳ ለረዥም ጊዜ ምላሽ ሳያገኝ ቆይቶ የነበረውን የሠራተኞች ወርሃዊ ደሞዝ የማሻሻል ጉዳይ በተመለከት፤ የድርጅቱ የገቢ ፍሰት በተጨባጭ መሻሻልን ተከትሎ ከሁለት እስከ አራት ዓመታት ምንም ማሻሻያ ላላገኙት የምርምርና የአስተዳደር ሠራተኞች በአማካይ የሃያ በመቶ (20%) ጭማሪ፤ በየዓመቱ ጭማሪ ሲደረግላቸው ለቆዩት ድጋፍ-ሰጭ ሠራተኞች ደግሞ የአስር በመቶ (10%) ጭማሪ እንዲደረግላቸው ያስተላለፈውን ውሳኔ ማኔጅመንቱ ከኖቬምበር ወር 2019 ጀምሮ በሥራ ላይ አውሏል። በዚህም መሰረት ከፍተኛ ወርሃዊ ደሞዝ ለሚያገኙት ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የአምስት በመቶ (5%) ጭማሪ ብቻ ሲደረግ፤ ለሦስት ዝቅተኛ የአስተዳደር ሠራተኞች ደግሞ ከሠላሳ በመቶ (30%) ያላነሰ ጭማሪ እንዲሁም ለተቀሩት የምርምርና የአስተዳደር ሠራተኞች በሙሉ አማካዩ የሃያ በመቶ (20%) ጭማሪ ተደርጓል። በየዓመቱ ጭማሪ ሲደረግላቸው ለቆዩት ድጋፍ-ሰጭ ሠራተኞች ደግሞ የአስር በመቶ (10%) ጭማሪ ተደርጎላቸዋል። የድርጅቱ ሠራተኞች በማኔጅመንቱ የተፈፀመውን የሥራ አመራር ቦርድ ውሳኔ ፍትሃዊ አተገባበር አስመልክተው በቀጥታ ለቦርዱ ሊቀመንበር ያቀረቡት ምስጋና ለ70ኛው የቦርዱ ስብሰባ ቀርቦ በስብሰባው ቃለ ጉባዔ እንዲሰፍር ሆኗል።

## 4. የድርጅቱ ሕንፃ ግንባታ ሂደት

ኤፍ. ኤስ. ኤስ. ደረጃዉን የጠበቀና በከተማዊ ማዕከላዊ ሊባል በሚችል ሰፊ ቦታ የራሱን ሕንፃ መሥራቱ የድርጅቱን ቀጣይነት በከፍተኛ ደራጃ ያረጋገጠ ቢሆንም ግንባታው ገና ብዙ ሥራዎች ስለሚቀሩት በአሁኑ ሰዓት የምድር ቤቱ ብቻ ባልተሟላ ሁኔታ ቢሆንም በጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል። ሕንፃውን አጠናቆ ለመጨረስ ብዙ ተጨማሪ ወጪን የሚጠይቅ እና መጭውን የበጀት ዓመት መጠበቅ የሚኖርበት ቢሆንም በዚህ ሪፖርት ዓመት አንዳንድ ለሕንፃው ደህንነት ወሳኝ የሆኑ የዝናብ ውኃ መውረጃዎችና የውጭ ቀለም ቅብ የመሳሰሉ መለስተኛ ወጭን የሚሹ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ድርጅቱ ከሕንፃው የማይገለገልባቸውን ክፍሎች ለተመሳሳይ ተግበራት ማከራየት የሚያስችሉት አንቀፆች በኤጀንሲው በፀደቀው የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ መካተታቸው የሕንፃውን የወደፊት ዕድልና ጠቃሚነት ይበልጥ ብሩኅ አድርጎታል።

## 5. የተጠናቀቁ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች

ጥናትና ምርምር ከኤፍ.ኤስ.ኤስ ዐቢይ ተግባራት መካከል አንዱ ሲሆን፤ በሪፖርት ዓመቱ ሁለት የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች ብቻ ተከናውነዋል። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ቀደም ባሉ የበጀት ዓመታት የተጀመረና ወደ ሪፖርት ዓመቱ የተሸጋገረ ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ በበጀት ዓመቱ ተቀርፃ የተተገበረ ነው። ኤፍ.ኤስ.ኤስ ተጨማሪ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን ያላከናወነበትን ምክንያት

በተመለከተ የዚህን ዘርፍ ቁልፍ ሚናነት ከመዘንጋት የመነጨ ሳይሆን ድርጅቱ ሳይታክት አንዳንዴ ራሱ እያፈላለገ ሌላ ጊዜ ደግሞ በቀጥታ እየተጋበዘ በብዙ ድካም አዘጋጅቶ ላስገባቸው ፕሮፖዛሎች በጎ ምላሽ ሳይቸረው በመቅረቱ ነው፡፡

## 5.1 የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች

### *5.1.1 የኢኮኖሚ ትስስር በሶማሊያ ምሥራቅ አፍሪካ Governing Economic Hubs and Flows in Somali East Africa (GOVSEA)*

ይኸ በሪፖርት ዓመቱ የተጠናቀቀው የአራት ዓመት የትብብር ፕሮጀክት በኤፍ.ኤስ.ኤስ እና ዴንማርክ አገር በሚገኘው የሮዝኪልድ ዩኒቨርሲቲ መካከል የተፈረመና በዳኒዳ ፌሎሺፕ ማዕከል (DANIDA Fellowship Center) የገንዘብ ድጋፍ የተካሄደ የጥናት ፕሮጀክት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ሶማሊላንድን፣ ፑንትላንድን እና የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚገኙባቸው የኢትዮጵያና ኬንያ ግዛቶችን ጨምሮ በሶማሊያ ምሥራቅ አፍሪካ አሁን ያለውን ቁልፍ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሒደቶችን በሚገባ መረዳትን ዋና ዓላማው አድርጎ የተቀረጸ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፕሮጀክቱ በአካባቢዎቹ ያሉት የዕለት ተዕለት የገበያ፣ የትራንስፖርትና የሸቀጥ እንቅስቃሴዎች በመንግሥት አወቃቀሮችና ሒደቶች ላይ ያላቸውን አንድምታ ይመለከታል፡፡ የጥናት ቡድኑ በፕ/ር ካሣሁን ብርሃኑ እና በዶ/ር አስናቀ ከፋለ የተመራ ነበር፡፡ በዚህ በሪፖርት ዓመቱ በተጠናቀቀው ፕሮጀክት ውስጥ የኤፍ.ኤስ.ኤስ. አይነተኛ ድርሻ ለጥናቱ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ የአስተዳደራዊና የሎጂስቲክ ድጋፍ መስጠት ሲሆን፤ ለዚህ አገልግሎቱም ከጠቅላላው 591,816.00 የዴንማርክ ክሮነር (ብር 2,223,621.00) በጀት ውስጥ 12 ከመቶ የአስተዳደራዊ በጀት አግኝቷል፡፡

### *5.1.2 የሴቶች ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ማብቃቶች፡- በገጠሩና በከተማው መካከል ያለውን የሴቶች ብቃትን የተመለከተ ንጽጽራዊ ጥናት (Women Social and Economic Empowerment: A comparative study between rural and urban households (በአባመላ ኮንሰልታንት)*

ጥናቱ ኤፍ.ኤስ.ኤስ ዝቅ ብሎ ከተወሳውና በጋራ ምህፃረ ቃል ሲ.ኤስ.ቲ (CST) ተብሎ ከሚጠራው ተቋም ጋር በኅብረት የሚያካሂደው ፕሮጀክት አካል ሆኖ በሪፖርቱ ዓመቱ የተከናወነ ነው፡፡ ጥናቱ የሴቶችን ማኅብራዊና ኢኮኖሚያዊ ብቃት በተመለከተ በገጠሩና በከተማው ክፍሎች መካከል ያሉትን ልዩነቶችና ተመሳሳይነቶችን የሚያመላክት ሲሆን በጥናቱም የተለያዩ ግኝቶች መታየት ችለዋል፡፡ ጥናቱ በዋንኛነት ያካተተው የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን ሲሆን የገጠሩን አካባቢ ለማመላከት በደቡብ አሪ፣ ቦረናና አምቦ አካባቢ የሚኖሩ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች መጠይቆችን በመሙላት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአንፃሩ፤ በመቀሌና በአዲስ አባባ የሚኖሩ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች የከተማውን ክፍል ወክለው ጥናቱ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ጥናቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ነክ ጉዳዮች የሚዳስሱ የብቃት መለኪያ ይዘቶችን ያካተተ ሲሆን አይነታዊና አሐዛዊ መጠይቆችን መሰረት በማድረግ ዋና የሆኑ ግኝቶችን ለአጋር ድርጅቶች አሳይቷል፡፡ የጥናቱን ግኝቶችን ለማመሳከርም ለግማሽ ቀን

የቆየ ውይይት የተደረገ ሲሆን በውይይቱም 17 የሚሆኑ ከአጋር ድርጅቶች የመጡ ግለሰቦች በተገኙበት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል። የጥናቱ ጠቅላላ ሪፖርትም ለሲ.ኤስ.ቲ. ደርሷል።

## 6. ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በጋራ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች

ኤፍ.ኤስ.ኤስ. በራሱ ከሚያካሂዳቸው ፕሮጀክቶች በተጨማሪ ተመሳሳይ ዓላማ ይዘው ከሚንቀሳቀሱ መሰል ድርጅቶች ጋር የጋራ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል። በዚህ መሠረት በሪፖርት ዓመቱ የሚከተሉት ፕሮጀክቶች ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በትብብር ተከናውነዋል።

### 6.1 ሴቶችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያብቃትን ለማዳበር የሚረዳ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት (Evidence-based capacity development project for women Socio-economic Empowerment)

ይህ ፕሮጀክት CAFOD, SCIAF እና Trocaire የካቶሊክ ቤተክርስትያን የልማት ድርጅቶች ጥምረት (በጋራ ምህፃረ ቃል ሲ.ኤስ.ቲ/CST ተብሎ ከሚጠራው) ተቋም ጋር ኤፍ.ኤስ.ኤስ በትብብር የሚያካሂደው ነው። ዓላማውም በመረጃ የተደገፈ ጥናትና ምርምር ላይ ተመሥርቶ የሴቶችን የማኅብራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ማዳበር ሲሆን፤ የውሳኔ ሰጪነት መብታቸውም እንዴት ሊዳብር እንደሚችል በተመለከተ ዘዴዎችን ለመጠቆምና የመፍትሔ እና የፖሊሲ ኃሳቦችን ለማመንጨት ያቀደ ነው። የአምስት ዓመት ፕሮጀክት የሆነው ይኸው ፕሮጀክት ሦስት የፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ዘርፎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም ምርምርና ጥናት እንዲሁም የአቅም ግንባታ ስልጠናዎቸን መስጠት ሲገኙበት በተለያዩ መንገዶች የተገኙትን ጠቋሚ መረጃዎችንም መሰረት በማድረግ በተለያዩ ሚዲያዎችና መድኮች በመጠቀም ለእብረተሰቡ ማድረስ ይገኙበታ። በዚህ መሠረት በሪፖርት ዓመቱ ኤፍ.ኤስ.ኤስ. ከሲ.ኤስ.ቲ ጋር በመሆን በብር 1,204,261.50 (አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ አራት ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ በር ከ ሀምሳ ሳንቲም) ጥናትና ምርምር፣ የአቅም ግምባታ ስልጠናና መረጃዎችን በኅብረተሰብ ዘንድ እንዲዳረስ ያደረገ ሲሆን ዝርዝሩንም በየሥራ መስኩ ርዕስ ስር ከታች ተመልክቷል።

*ጥናትና ምርምር፦*

በተገባደደው ዓመት በፕሮጀክቱ ከላይ በ5.2.1 ስር የተወሳው የሴቶችን ማኅብራዊና ኢኮኖሚያዊ ብቃት በተመለከት በገጠሩና በከተማው ክፍሎች መካከል ያሉትን ልዩነቶችና ተመሳሳይነቶችን የሚያመላክት ምርምር እንዲካሄድ አድርጎ ለፍሬ አብቅቷል።

*የአቅም ግንባታ ስልጠና፦*

በሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ተለዋጭ የፆታ ሥርዓቶች ላይ ያተኮረ የሦስት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ለስምንት የሲ.ኤስ.ቲ አጋር ድርጅቶች የተሰጠ ሲሆን፤ በስልጠናውም 32 የአጋር ድርጅቶቹ ሠራተኞች ተሳትፈዋል። የስልጠናው ዋና ይዘት የቤተሰብን የሥራ ድርሻ በተመለከተ እና የተሳካ ኑሮን ለመምራት የሚረዳ የራዕይ አነዳደፍ ዘዴዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን የሲ.ኤስ.ቲ ተጠቃሚዎችን በኢኮኖሚው እና ማኅብራዊው ዘርፎች ብቃታቸውን ለማሳደግ ከግል ሂወት አንስቶ የቤተሰብን እና የአካባቢን ልማት ለማሳደግ የሚየስችሉ ርእሶችን አካቷል።

ስልጠናው ንቁ ተሳትፎን መሰረት ከማድረጉም በላይ በስልጠናው መጨረሻ ቀን ሰልጣኞች የመስክ ተግባራዊ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ ተጠናቋል፡፡

### 6.2 የአየር ንብረት ለውጥና የሰዎች እንቅስቃሴ (Governing Climate Mobility - GCM)

ባለፈው የሪፖርት ዓመት ኤፍ.ኤስ.ኤስ *Governing Climate Mobility (GCM)* የተሰኘ የአራት ዓመት ፕሮግራም ከዴማርክ አለም አቀፍ ጥናት ኢንስቲትዩት Danish Institute of International Studies - DIIS) እና ከጋና ዩኒቨርስቲ የፍልሠት ጥናት ማዕከል (Centre for Migration Studies - CMS) ጋር የሚተገበር የሦስትዮሽ የአራት ዓመት የጥናት፣ ምርምርና ሕትመት ፕሮጀክት መፈራረሙ ይታወሳል፡፡ የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ በአየር ንብረት ለውጥና በሰዎች ፍለሠት መካከል ያለውን ቁርኝት በማጥናት የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ነገሮች ለመቋቋም የሚያስችል ሳይንሳዊ ንድፈ-ኃሳብ ማውጣት ነው፡፡ በፕሮግራሙ ዝርዝር ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት በሪፖርት ዓመቱ የተለያዩ የቅድመ-መስክ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን እና በኦሮሚያ ክልል ደቡብ አርሲ ዞን የመስክ ስፍራ መረጣ ፊልድወርክ ተካሂዷል፡፡ ቅድመ-መረጣ መረጃዎች ተሠብስበው ተተንትነዋል፡፡
- በፕሮግራሙ የሚሳተፉ ዶክተሬት ተማሪዎች ማስታወቂያ በማውጣት በማወዳደር የተመረጡ ሲሆን በመስከረም 2012 ትምሕርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡
- ዴንማርክ፣ ጋና እና ኢትዮጵያ ያሉ ሁሉም ተመራማሪዎች የተሳተፉበት ሁለት የቅድመ-መስክ ሥራ ዎርከሾፖች በኮፐንሀግን (ዴንማርክ) እና በአዲስ አበባ ተካሂደዋል፡ ፡ የአዲስ አበባው ወርክሾፕ በድርጅታችን አስተናጋጅነት የተካሄደ ሲሆን ከጥቅምት 24 እስከ 28 ቀን 2012 የተካሄደ ነበር፡፡
- አንድ ሳምንት (ከሕዳር 30 እስከ ታህሳስ 5 ቀን 2012) የፈጀ ሁሉም ተመራማሪዎችና ዶክተሬት ተማሪዎች የተሳተፉበት የመስክ መረጃ ስብሰባ ሥራ በደቡብ አርሲ ዞን ሻሸመኔና አካባቢዋ ተካሂዷል፡፡
- ለሚቀጥለው የበጀት ዓመት የመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያዎች (data collection instruments) እና ዝርዝር የሥራ ዕቅድ ወጥቶ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

## 7. የህዝባዊ ውይይት መድረክ መርሃ-ግብር

በተለምዶ፤ ኤፍ.ኤስ.ኤስ ሁለት ዓይነት የውይይት መድረኮች ያካሄዳል፡፡ አንደኛው አይነት የውይይት መድረክ ከጥናት ፕሮጀክት ጋር ተያይዞ የጥናት ውጤቶችን ለባለድርሻ አካላት ለማቅረብ በስተመጨረሻ አንድ ጊዜ ብቻ የሚዘጋጅ የውይይት መድረክ ሲሆን ሁለተኛው ራሱን የቻለ የውይይት መድረክ ፕሮጀክት ሆኖ ከ1-2 ዓመት የሚዘልቅና ፕሮግራም ተይዞለት

በበርካታ የፖሊሲ ርዕስ ዙሪያ የሚዘጋጅ የውይይት መድረክ ነው። በዚህ ሪፖርት ዓመት፤ ኤፍ.ኤስ.ኤስ ሁለት የሁለተኛው ዓይነት የውይይት መድረኮችን ብቻ አካሄዷል።

### 7.1 ዲሞክራሲያዊ ጉዞ ለውጦች፡- በዋና ዋና አገራዊ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ለውጦች ላይ የሚደረግ የሕዝባዊ ውይይት መድረክ (Clarifying the Uncharted Routes of Ethiopia's Transition towards Democracy:...)

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ባልተለመደ የለውጥ ሒደት ውስጥ መሆኗ ቢታወቅም ይህ የለውጥ ሒደት ወዴት አቅጣጫ እንደሚያመራ በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም። በመሆኑም ይህን ለውጥ በተመለከተ በተለያዩ የኅብረተሰብ አካላት የሚሳተፉበት ውይይት ማድረግና አማራጮችን መመልከት አስፈላጊነቱ አያጠራጥርም። በመሆኑም ኤፍ.ኤስ.ኤስ የጉዳዩን ወቅታዊነትና አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት መካከል በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውይይት የሚደረግበት ሕዝባዊ የውይይት መድረክ አዘጋጅቷል። ሕዝባዊ የውይይት መድረኩ በየአንድ ወር ከአሥራ አምስት ቀኑ በመካሄድ ለስምንት ወራት ያክል የሚዘልቅ ሲሆን፤ በስድስት መሪ ርዕሶች ላይ የሚያተኩሩ ስድት መድረኮች ይዘጋጃሉ። በእያንዳንዱ መድረክ ላይም የተለያዩ ኃሳቦችን የሚያንጸባርቁ ሁለት ሁለት የውይይት ወረቀቶች የሚቀርቡበት የግማሽ ቀን የውይይት ፕሮግራም የሚካሄድ ከመሆኑ በላይ ፕሮጀክቱ ሦስት የሕትመት ውጤቶች ይይዛል። እነዚህም 1ኛ) ሕዝባዊ የውይይት መድረኩ ማስተዋወቂያ በራሪ ወረቀት፣ 2ኛ) የእያንዳንዱን መድረክ መጠናቀቅ ተከትሎ የሚታተሙ በየውይይት መድረኩ የቀረቡ ስድሰት የጥናት ጽሁፎች በdiscussion paper መልክና 3ኛ) በሁሉም መድረኮች የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች አርትዖት ተድረጎባቸውና ተስተካክለው በመጽሐፍ (workshop proceding) መልክ በኤሌክትሮኒክ (electronic version) ይሆናሉ። እንዲሁም ኤፍ.ኤስ.ኤስ በየመድረኮቹ የሚደረጉትን ውይይቶች በተካሄዱ በሁለት ሳምንታት ውስጥ በራሱ የሬድዮ ፕሮግራምና በብሔራዊ ሬዲዮ ጣቢያ ለሕዝብ የሚያቀርብ ከመሆኑ በተጨማሪ የውይይቶቹን ፍሬ ኃሳቦች በሳምንታዊው *የሪፖርተር ጋዜጣ* በማሳተም ለሕዝብ ያቀርባል። 45,000.00 የአሜሪካን ዶላር (ብር 1,260,000 ገደማ) የሚጠይቀው ፕሮጀክ የረጂም ጊዜ አጋራችን በሆነው ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ (*National Endowment for Democracy* - NED) ለጋሽ ድርጅት ቀርቦ ተቀባይነት በማግኘቱ የፕሮጀክቱ ትግበራው እ.ኤ.አ. በኤፕሪል 1 ቀን 2019 ተጀምሮ በዲሴምበር 31ቀን 2019 እንዲጠናቀቅ ተወጥኖ ነበር። ሆኖም ሥራዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች በመጉዋተታቸው የተነሳ ተደጋጋሚ ከዋጋ ጭማሪ ነፃ የሆኑ የጊዜ ገደብ መራዘም (no-cost extension) ተችሮት ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ. በሐምሌ 2020 በአጥጋቢ ደራጃ ተገባዷል።

### 7.2 መሬት፤ የመሬት አጠቃቀም እና የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ:- ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ (Land, Land Utilization and Food Security in Ethopia: A Public Dialogue Forum Series) ከታህሳስ 16 – መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም (26th December 2019 — 2nd April 2020)

ኤፍ.ኤስ.ኤስ. ባለፉት ሃያ ዓመታት ሲያደርገው እንደቆየው ሁሉ አንገብጋቢ እና ወቅታዊ በሆነው የመሬት ጉዳይ ላይ፤ **"መሬት፣ የመሬት አጠቃቀምና የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ"** በተሰኘ ዓቢይ ርዕስ ስር ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት እና ለአራት ወራት ማለትም ከታህሳስ 16 እስከ መጋቢት 24 2012 (26th December 2019 — 2nd April 2020) የሚዘልቅ ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ መርሀግብር አዘጋጅቶ በሪፖርት ዓመቱ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል፡፡

በዚህ በኦ.ሲ.ኢ.አ (Open Society Initiative for East Africa — OSIEA) የገንዘብ ዕርዳታ የተደገፈ መርሃ-ግብር፤ ሀ/ አገር አቀፍ የመሬት እና የምግብ ዋስትና ጉዳዮችን በተመለከተ በስድስት የተመረጡ ርዕሶች ላይ በአዲስ አበባ ለ/ እንዲሁም አሳሳቢ በሆኑ ክልል-ተኮር ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በሦስት ክልሎች (በኦሮሚያ፣ ትግራይ እና አማራ)፤ በአጠቃላይ ዘጠኝ ዝግጅቶች የሚካሄዱ ሲሆን በእያንዳንዱ መድረክ ላይም ለውይይቶቹ መነሻ የሚሆኑ ጥናታዊ ፅሑፎች በየዘርፉ ባለሙያዎች ቀርበው አስተያየት ይሰጥባቸዋል፤ በአገር ቋንቋዎች የቀረቡ ፅሑፎቹ እና በእንግሊዝኛ የሚወጡት አጫጭር የፍሬ ኃሳብ መጣጥፎቻቸው በኤሌክትሮኒክት ሚዲያ፣ በሕትመት እና በኤፍ.ኤስ.ኤስ ድረ-ገፅ አማካይነት ለሕዝብ በሰፊው ይተላለፋሉ፡፡ በዚህም መሠረት፣ የመርሀ ግብሩ መክፈቻ በሆነው ዝግጅት ላይ *"የገጠር መሬት ሥሪት በኢትዩጵያ"* የተሰኘ ፅሑፍ በታህሳስ 16 ቀን 2012 ዓ.ም በአቶ ደሳለኝ ራህማቶ ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡ ቀሪዎቹ ስምንት መድረኮችም በሚመጣው የሪፖርት ዓመት ይካሄዳሉ፡፡

## 8. የሚዲያ ሥርጭት እና የኮምዩኒኬሽን መርሃ-ግብር

የሚዲያ ሥርጭትና የኮምዩኒኬሽን መርሃ-ግብር ኤፍ.ኤስ.ኤስ የተቋቋመባቸዉን ዓላማዎች ለማሳካት ከዘረጋቸው ቁልፍ የሥራ ዘርፎች አንዱ ሲሆን፤ የሥራ ዘርፉ የሚያከናውናቸው ተግባራት በሁለት ዓይነት አግባብ ይካሄዳሉ፡፡ እነሱም፤ ሀ/ አንደኛው ድርጅቱ በሌሎች የተለያዩ የሥራ ዘርፎቹ ከሚያካሂዳቸው የጥናትና/ምርምር ሥራዎች እና ከሚያዘጋጃቸው ህዝባዊ የውይይት መድረኮች የሚፈልቁ ውጤቶችን የሚያሠራጭበት ራሱን የቻለ መርሃ-ግብር ሲሆን ለ/ ሁለተኛው ደግሞ ኤፍ.ኤስ.ኤስ ከተባባሪ ድርጅቶቹ ጋር በመሆን በሚተገብራቸዉ የተለያዩ ፕሮጀክቸቶች ውስጥ ውጤቶቻቸው በብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ለባለ ድርሻ አካላት እና ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ተካትተው በመቀረፃቸው በዚሁ መሠረት የሚሠራበት አግባብ ነው፡፡ የሥራ ዘርፉ በተጠናቀቀው የሪፖርቱ ዓመት፤ ሁለት የመጀመሪያው ዓይነት የሚዲያና ኮምዩኒኬሽን ፕሮጀክትን የተገበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የሁለተኛው ዓይነት፤ ማለትም ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር የተያዙ የሚድያ ሥርጭት ፕሮገራሞችን በትብብር ሰርቷል፡፡

### 8.1 **የኤፍ.ኤስ.ኤስ የጥናት/ምርምር እና የውይይት መድረክ ውጤቶች የሚዲያ ሥርጭት ፕሮጀክት** (Dissemination of FSS Research and Dialogue Outputs through the Media)

ይህ ፕሮጄክት ኤፍ.ኤስ.ኤስ በየዓመቱ ከናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ (National Endowment for Democracy - NED) የገንዘብ ድጋፍ ሲተገበር የቆየ የሚድያ ፕሮጄክት ሲሆን በሪፖርት ዓመቱ በእቅድ ከውተያዙት የሬድዮ ፕሮግራሞች ዉስጥ 75 በመቶ የሚሆኑት፤

- 30 ሳምንታዊ ፕሮግራሞች በኤፍ ኤም አዲሰ FM 97.1
- 30 ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ደግሞ በፋና ሻሸመኔ ኤፍ.ኤም (FM 93.43) ተላልፈዋል፡፡
- በተጨማሪ፤ 6 ፅሁፎች በአማርኛ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ታትመው ተሠራጭተዋል፡፡

### 8.2 **ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች፥ እንድምታዎቻቸው እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ** … (Clarifying the Uncharted Routes of Ethiopia's Transition towards Democracy:…) በተሰኘው ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ፕሮጀክት አካል በመሆን በተካሄዱት የውይይት መድረኮች ላይ የተመሰረቱ የሬዲዩ ፕሮግራሞች ለሕዝብ ተደራሽ ሆነዋል፡፡

- በዚህም መሠረት በፕሮጀክቱ በእቅድ ከተያዙ 13 ሳምንታዊ የሬዲዩ ፕሮግራሞች ውስጥ 10 ፕሮግራሞች በሪፖርት ዓመቱ ዉስጥ ተሠራጭተዋል፡፡
- በተጨማሪም 10 የዉይይት ፕሮግራም ቪድዮ ክሊፖች በዩቲውብ ተጭነው ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

### 8.3 **የዋይድ ሕዝባዊ ግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሚዲያ ሥርጭት ፕሮጀክት** (WIDE Awareness and Media Dissemination Project) **በኤፍ.ኤስ.ኤስ እና በ"Ethiopia-WIDE: Well-Being Ill-Being Dynamics in Ethiopia** በተሰኘ አጋር የጥናት ማዕከል በመተባበር የተካሄደ ሲሆን፤ የጥናት ማዕከሉ በተለያዩ የልማትና ልማት-ነክ ጉዳዮች ከ20 ዓመት በላይ በወሰደ ግዜ ያካሄዳቸው ጥናት ዉጤቶች ቀጥለው በተዘረዘሩት የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ለሕዝብ ተደራሽ ሆነዋል፡፡

- 13 የግማሽ ሠዓት ሳምንታዊ የሬዲዩ ፕሮግራሞች በኢትዩጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፓሬት (ኢ.ቢ.ሲ) ብሄራዊ ድምፅ ተላልፈዋል፤
- 6 ሙሉ ገፅ የጋዜጣ ፅሁፎች በሪፖርተር ጋዜጣ ታትመዉ ለአንባቢያን ቀርበዋል፤
- 4 አጫጭር የቴሌቪዥን ፕሮግሞች በዋልታ ቴሌቪዥን ተላልፈዋል፡፡

8.4 **ከ** CAFOD, SCIAF, Trocaire (CST) **ጋር በመተባበር በሚተገበረው በሴቶች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብቃትን ለማዳበር የሚረዳ በመረጃ ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ** (Evidence-based Capacity Development Project for Women Socio-economic Empowerment) **ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ፤**

- 13 የ30 ደቂቃ ሳምንታዊ የራድዮ ፕሮግራሞች በፋና ብሮድካስቲግ ኮርፓሬት (FBC) ተላልፈዋል።
- 3 ሙሉ ገፅ ፅሁፎች በአማርኛ ሪፖርተር ጋዜጣ ታትመው ለአንባቢ ተደራሽ ሆነዋል።

**በአጠቃላይ፤** በተጠናቀቀው የሪፖርቱ ዓመት (2019) በመርሃ-ግብሩ

- ➢ 96 ሳምንታዊ የሬድዩ ፕሮግራሞች
- ➢ 15 የጋዜጣ ፅሁፎች
- ➢ 4 የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች

ለሕዝብ ቀርበዋል። በመሆኑም፥ የሪፖርት ዓመቱ በሚድያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ አጥጋቢ እንቅስቃሴ የተደረገበት ሲሆን፤ በተጨማሪ፥ ኤፍ.ኤስ.ኤስ በታሪኩ ለመጀመርያ ግዜ ቴሌቪዥንን በሚድያ ሥርጭት መሳርያነት መጠቀም የጀመረበት ዓመት እንደ ነበር ሊወሳ ይገባል።

በተጨማሪ፥ በሚመጣው ዓመት በተለያዩ የጥናት የዉይይትና የአቅም ግንባታ ሥራ ዉጤቶች ላይ የተመሰረቱ የሚድያ ፕሮግራሞችን በይበልጥ በኤፍ.ኤስ.ኤስ ድረ-ገፅ እና ማኅብራዊ ሚዲያ አማካኝነት ለሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ አስፈላጊውን ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ከወዲሁ ማስታወቅ ይቻላል።

# 9. የሕትመትና የኦድዮ-ቪድዮ ሥራዎች

## 9.1 መጻሕፍትና ሞኖግራፎች

በሪፖርት ዓመቱ የሚከተሉት መጻሕፍትና ሞኖግራፎች ታትመው ለሕዝብ ተሠራጭተዋል።

1. ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች እንድምታዎቻቸው እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ -- (ቅፅ 1) ሕግ መንግሥት ብሔር-ተኮር ፌዴራሊዝም የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሕዝባዊ ምርጫ -- በዶ/ር አሰፋ ፍስሃ፥ ዶ/ር ዘመላክ አይተነው፥ ፕ/ር ካሣሁን ብርሀኑ እና ዶ/ር ዮናስ አሸኔ

## 9.2 የፖሊሲ ፍሬ ኃሳብ ሕትመት (Policy Briefs)

በኤፍ.ኤስ.ኤስ. የቆየ ልምድ መሠረት የፖሊሲ ፍሬ ኃሳብ ረጅም የጥናት ውጤት ሕትመቶችን ለማንበብ ጊዜ ለማይኖራቸው የፖሊሲ አውጪዎች እና ሌሎች አካላት በአጭሩ ተዘጋጅቶ የሚሠራጭ ጠቃሚ ሕትመት ነው። ሆኖም፤ በሪፖርት ዓመቱ ውስጥ እንድም የተካሄዱት ሥራዎች የፖሊሲ ፍሬ ኃሳብ ሕትመት የማያስፈልጋቸው በመሆናቸው ወይም እየተጠበቁ ያሉ የፖሊሲ ፍሬ ኃሳብ ሕትመቶች በመዘግየታቸው የተነሳ፤ የተሠራጨ የፖሊሲ ፍሬ ኃሳብ የለም።

### 9.3 ብሮሹር እና ኦዲዮ-ቪዲዮ

1. ሕዝባዊ የውይይት መድረክ -- ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች እንድምታዎቻቸው እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ (የተከታታይ መርሃ-ግብሩ መግለጫ እና የታቀዱትን ስድስት መድረኮች ዝርዝር ፕሮግራም የያዘ ብሮሸር)
2. ሕዝባዊ የውይይት መድረክ -- መሬት፤ የመሬት አጠቃቀም እና የምግብ ዋስትና በኢትዮጵያ (የተከታታይ መርሃ-ግብሩ መግለጫ እና የታቀዱትን ዘጠኝ መድረኮች ዝርዝር ፕሮግራም የያዘ ብሮሸር)
3. 13 የWIDE፤ 13 የበሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት, 10 የዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች፥ እንድምታዎቻቸው እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ፤ በጠቅላላ 36 ውጤቶች የያዙ ዩቲዩቦች ከነባሩ የኤፍ.ኤስ.ኤስ ድረ-ገፅ ጋር በመያያዝ ተሠራጭተዋል።

### 9.4 *የአፍሪካ መፅሐፍት ግምገማ* (African Review of Books-ARB)

African Review of Books በእንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎች እየተዘጋጀ ከአፍሪካ ማኅበራዊ ሳይንስ ጥናት ማዕከል (CODESRIA) ጋር በመተባበር የሚዘጋጅ ሕትመት ሲሆን፣ በአፍሪካ አህጉር ላይ የሚያተኩሩ በመላው አለም የታተሙ መፅሐፍቶች ላይ የሚያተኩር ነው። ኤፍ.ኤስ.ኤስ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በዋና አዘጋጅነት ሲያገለግል የቆየ ሲሆን በዚህ ረጅም ጊዜ ሕትመቱን በወረቀት እና በሶፍት ኮፒ አሠራጭቷል። ሆኖም የሪፖርት ዓመቱ በሆነው እ.ኤ.አ. 2019 ሥራው እጅግ ውስብስብና ፈታኝ እየሆነ በመምጣቱ ድርጅታችን ኃላፊነቱን ለ CODESRIA መልሷል።

## 10. የቤተ-መፅሀፍት እና የዲጂታል ኮሚኒኬሽን አገልግሎት

የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ቤተ-መፅሀፍት ከራሱ ድርጅት አልፎ ለተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት፣ ውሳኔ ሰጪ አካላት፣ እንዲሁም መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እና ተመራማሪዎች ጠቃሚ የመረጃና የዕውቀት መገኛ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል። የቤተ-መፅሀፍቱ አትኩሮት በአጠቃላይ ልማት-ነክ ጉዳዮች ላይ ሲሆን፤ ትምህርት፣ ጤና፣ ግብርና፣ የመሬት ጉዳዮች፣ ድህነት፣ ሥነ-ፆታ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ በምግብ ራስን መቻል፣ ወዘተ ... ናቸው። ቤተ-መፅሀፍቱ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ምቹ የማንበቢያ ቦታ፣ ተደራሽ የቤተ-መፅሀፍት ስብስቦች፣ ነፃ የፎቶ ኮፒ እና የኢንተርኔት አገልግሎት ይገኛሉ።

እንደሚታወቀው ከዚህ በፊት የነበረው አጠቃላይ የቤተ-መፅሀፍት አጠቃቀም እና አገልግሎት በቴክኖሎጂ ምክንያት እየተለወጠ ስለመጣ ድርጅታችን ይህንን ለውጥ በመከተል የመረጃ ቋቱንና የማሠራጫ መንገዶቹን የግድ ማዘመን ይኖርበታል። በመሆኑም የቤተ-መፅሀፍቱና እና ባሁኑ ጊዜ ከመኖር የማይቆጠረውን ድረ-ገፁን እና ተቋርጦ የነበረውን ዲጂታል ሪፖዚተሪውን ከፍተኛ የገንዘብ ፈሰስ በማድረግ በሚቀጥለው ዓመት መጀመሪያ ላይ በአዲስ መልክ ለመሥራት በዝግጅት ላይ እንገኛለን። እየተገለገልንበት ያለው የድርጅታችን ድረ-ገፅ ከተሠራ ከ10 ዓመት በላይ ስለሆነውና ለተጠቃሚዎች አመቺ ሆኖ ባለመገኘቱ የተሻለ መርጃ ከተሻለ

ፍጥነት ጋር እንዲሰጥ በአዲስ መልክ ለማሠራት ታቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን በቅርቡም ሥራው ይጀመራል፡

በተጨማሪ፤ የድርጅቱን ሠራ ውጤቶች ተደራሽነት ለማስፋት ሲባልም ድርጅታችን የተለያዩ የማኀበረሰብ ትስስር ገፆችን ጭምር በስፋት ለመጠቀም ተዘጋጅቷል። ይህም እርምጃ በድርጅታችን ስር በተለየዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናት ውጤቶችን፣ የተደረጉ የህዝባዊ ውይይት መድረኮችን እንዲሁም በተለየዩ ጊዜያት የተላለፉ የራዲዮ ፕሮግራሞችን በስፋት ለማሠራጨት እንደሚረዳ አያጠራጥርም። ከዚህ ጋራ ተያይዞም የቤተ-መፅሀፍት ባለሙያ የሥራ ዘርፉችን ከመፃሕፍት ቤቱ በተጨማሪ የዲጂታል ኮሚኒኬሽን ሥራውንም እንዲያጠቃልል ሆኖ ተስተካክሏል። በሪፖርት ዓመቱ 54 የሚሆኑ አዳዲስ ሕትመቶች ወደ ቤተ-መፅሀፍታችን ገብተዋል።

## 11. የውጭ ትብብር እና ተሳትፎ

ኤፍ.ኤስ.ኤስ. ከመንግሥት፣ ሲቪል ማህረሰብ ድርጅቶች፣ ከአካዳሚክ፣ ከግል ማኀበረሰብና ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ፍሬያማ ትብብርና አጋርነት እንዲኖር በተለያዩ መድረኮች ይሳተፋል። እነዚህ ኤፍ.ኤስ.ኤስ በተጋባዥነት የተሳተፈባቸው መድረኮች በርካታ ሲሆኑ በዚህ ሪፖርት ድርጅቱ እ.ኤ.አ 2019 በንቃት የተሳተፈባቸው የውይይት መድረኮች ብቻ ተመርጠው በጥቅል በጥቅሉ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ገበታ ሰፍረዋል።

| ተ.ቁ | ተሳትፎ | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ከአጋር ድርጅቶች ጋር የተደረጉ ስብሰባዎች እና አውደጥናቶች | 8 |
| 2 | በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ አማካይነት በተደረጉ ስብሰባዎች እና አውደጥናቶች | 4 |
| 3 | ንግግር የተደረጉባቸው የጠ/ሚ/ቢሮ “አዲስ ወግ”፣ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት እና በሲ.ሲ.ር.ድ.ኤ በተዘጋጀው የሲቪል ማህበረሰብ ለሰላም ስብሰባዎች | 3 |
| 4 | በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ “አዲስ ወግ” እና ሌሎች ስብሰባዎች | 5 |
| 5 | የተለያዩ ኮንፈረንሶችና አውደጥናቶች | 15 |
| 6 | በውጭ ሀገራት በተካሄዱ ሁለትየIGAD/CEWARN Training እና በIOM Thematic Meeting on Remittance | 3 |
| | **ድምር** | **38** |

## 12. ጥንካሬ፣ ያጋጠሙ መልካም አጋጣሚዎች እና ተግዳሮት

ይህ ሪፖርት በተጠናቀረበት ወቅት በመቀጠል የተዘረዘሩት ጥንካሬዎች ፣ እድሎችና ተግዳሮት በሥራችን ላይ ተፅእኖ ፈጥረው ነበር።

**ጥንካሬያችን፡-**

- በሪፖርት ዓመቱ ኤፍ.ኤስ.ኤስ የቆመላቸውን ተግባራት በነፃነት እና በሚገባ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለውን የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንቡን አርቅቆ እና በሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኤጀንሲ አፀድቆ የሕጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀት ባለቤት መሆኑ ድርጅታዊ ቁመናውን አጠናክሮታል።

- በሪፖርት ዓመቱ በብዙ ድካም እና በከፍተኛ ወጭ የተተገበረው የኢ.ፐ.ሳ.ስ (IPSAS) ሂሳብ አያያዝ በእጅጉ ቁጥጥረ-ጥብቅ እና ሁሉ-አቀፍ በመሆኑ፤ አተገባበሩ የጠየቀውን መስዋዕትነት የሚመጥን ብቻ ሳይሆን፤ ለድርጅቱ ግልፅ፥ ጥብቅ እና ቋሚ የገንዘብ እና የንብረት አያያዝ ሥርዓት ዘርግቷል።

- ኤፍ.ኤስ.ኤስ እንደ ኦ.ሲ.አ (Open Society Initiative for East Africa — OSIEA) ያሉ ፕሮግራሞቹን ለመደገፍ እና አቅሙን ለመገንባት በጎ ፈቃድ ያላቸውን አዳዲስ አጋሮች አግኝቷል።

- ኤፍ.ኤስ.ኤስ በምሁራን፣ በተመራማሪዎች፣ ከመንግሥታዊ እና ከሲቪክ ማኅበራት በተገኙ ዓባላት የተመሰረተ ድርጅት በመሆኑ፤ ዓባላቱን እና እነሱ ያሏቸውን የትብብር መረቦች ተጠቅሞ በልማት ላይ ያተኮሩ ዘርፈ ብዙ የፖሊሲ ጥናቶች እና የውይይት መድረክ መርሃ-ግብሮቹን በሚገባ ለመተግበር የሚያስችል ጠንካራ አቅም አለው።

- ኤፍ.ኤስ.ኤስ በሠራቸው ልማት ላይ ባተኮሩና ጥራት ባላቸው የጥናትና ምርምር ሥራዎቹ እና በተለይም በሪፖርት ዓመቱ በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ባካሄዳቸው ህዝባዊ ውይይቶች አማካይነት ከዚህ ቀደም የተቀዳጃቸውን ክብርና እውቅና በማስጠበቅ በአገሪቱ ካሉት ጥቂት ግንባር ቀደም የዕውቀት እና የኃሳብ አመንጭ ማዕከሎች አንዱ በመሆን ቀጥሏል።

**መልካም አጋጣሚዎች፡-**

- በቅርቡ ፀድቆ የወጣው የሲቪል ማኅበራት አዋጅ በፈጠረው ሰፊ አሰሪ ሜዳ እና የአዋጁ ዋነኛ አስፈፃሚ ተቋም በሆነው በሲል ማኅበራት ድርጅቶች ኤጀንሲ ለሙያ ማኅበራት እና ሀሳብ አፍላቂ ድርጅቶች የያዘው ቀና አመለካከት፤ ኤፍ.ኤስ.ኤስን በተሻለ ደራጃ ለመንቀሳቀስ አስችለውታል።

- አዲሱ የሲቪል ማኅበራት አዋጅ የፈጠረው ምህዳር ለኤፍ.ኤስ.ኤስ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ገንዘብ ማግኘት የሚያስችል ዕድልን ፈጥሮለታል።

- በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘው የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ለቤት ኪራይ ይከፈል የነበረውን ወጭ በማስቀረቱ የድርጅቱን ዘላቂ ህልውና ያረገገጠ ስኬት ሆኗል፡፡

**ተግዳሮት፡-**

- ምንም እንኳን የሲቪል ማኅብራት አዋጁን ጨምሮ አገራችን ያለችበት የለውጥ እና የዲሞክራሲ ምህዳር ለድርጅቱ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን በመፍጠር ላይ ያለ ቢሆንም፥ ከለውጡ ጋር ተያይዞ የመጣው የሰላም መደፍረስ እና የደኅንነት እጦት በድርጅቱ ሥራዎች ላይ የተወሰነ የማዘግየት ተፅእኖ በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡
- በተመሳሳይ፤ በሪፖርቱ ዓመት የመጨረሻ ወራት በዓለማችን ላይ ብቅ ያለው የኮሮና-19 ወረርሺኝ በድርጀቱ የምርምር እና የውይይት መርሃ-ግብሮች አፈፃፀም እና ወጭን በተመለከተ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ የስከትላል ተብሎ በሥጋት ይጠበቃል፡፡
- የድርጅቱ ገቢዎች በሙሉ ከተቀረፁ ፕሮጅክቶች ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው እና ከፕሮጀክቶች ያልተያያዘ የአቅም ግንባታ ወይንም የመሸጋገርያ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት የማይሞከር እየሆነ መምጣቱ ችግር እንደቀጠለ ነው፡፡
- አባላት በድርጅቱ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ውስንነት ለምሳሌም በምናዘጋጃቸው የተለያዩ ሕዝባዊ ውይይቶች፣ ወርክሾፖች፣ የሪሰርች ውጤቶችን ማስተዋወቂያ መድረኮች ላይ ያለመገኘት አሳሳቢ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡

**ማጠቃለያ፡-**

ድርጅቱ በሪፖርት ዓመቱ ሥርዓታዊ እና ሕጋዊ አቋሙን ከመቸውም በበለጠ ደረጃ አስተካክሏል፤ አመቺ የሥራ አካባቢ ተፈጥሮለት በርካታ መደበኛ ተግባራቱን በሚገባ አከናውኗል፤ ከፕሮጄክቶች ጋር አያይዘው ለአቅም ግንባታው ድጋፍ የሚሰጡ አጋሮችም አግኝቶ ሠራተኞቹን ሁኔታም በማይናቅ ደራጃ አሻሽሏል፡፡ በመሆኑም፤ በዋነኛነት በዓመቱ መገባደጃ ላይ ብቅ ያሉት የሰላም መደፍረስ እና የኮሮና-19 ወረርሺኝ የጋርጡበትን ተግዳሮት በብልሃት እየተወጣ በመንቀሳቀስ የዘንድሮው ስኬቶቹ በመጭው ዓመት ፍሬ እንዲሰጡ እንደሚያደርግ ዕሙን ነው፡፡

